## ካምብሪጅ የህዝብ ትምህርት ቤቶች

# የኮቪድ 19

## ምርመራ እና የኳራንቲን

# ፕሮቶኮሎች

## ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች


ገጽ 1:- የህመም ምልክቶች ዝርዝር እና የምርመራ ማጠቃለያ
ገጽ 2:- አዎንታዊ ውጤት ያላቸው ጉዳዮችን የሚገለሉበት የጊዜ ሰሌዳ
ገጽ 3:- ከትምህርት ቤት ውጭ አዎንታዊ የምርመራ ውጤት ያላቸው በተመለከተ፡ የቅርብ ተጠሪ አካል
ገጽ 4:- የጉዞ መመሪያዎች


# ምርመራ

**የተፈረመ የፈቃድ ቅጽ በማሳየት**: ተማሪዎች በሶስት ዓይነት የኮቪድ-19 ምርመራዎች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ:-

- **በትምህርት ቤት:-** በቀን ላይ የሕመም ምልክቶችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች የሚደረግ ምልክት ያላቸው (symptomatic) ምርመራዎች
- **በትምህርት ቤት:-** በየሳምንቱ የሚደረጉ የፑል ምርመራዎች፡ የህመም ምልክት የሌላቸው (asymptomatic) ጉዳዮችን ለይቶ ለማሳየት
- **በቤት ውስጥ:-** ፈጣን ምርመራዎች፡ የህመም ምልክት የሌላቸው (asymptomatic) ጉዳዮችን ለይቶ ለማሳየት

የሚሞሉ ቅጾች በሙሉ በዚህ የ CPS የቤተሰብ ፖርታል በኩል ይሞሉ:-https://secure1.cpsd.us/family_portal

# ምልክቶች

## እነዚህ የህመም ምልክቶች ካሳዩ:-

- ➔ እቤት ውስጥ ይቆዩ
- ➔ በቤት ውስጥ ወይም በማህበረሰብ ማእከል ይመረመሩ
- ➔ **አሉታዊ የምርመራ ውጤት ካገኙ (PCR ወይም ፈጣን ምርመራ) በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሱ። CPS የአሉታዊ የምርመራ ውጤት ማረጋገጫ አይፈልግም።**

- ከ 100.0 ዲግሪ ፋራናይት በላይ ትኩሳት
- ብርድ ብርድ ማለት፣ ወይም የሚንቀጠቀጥ ብርድ
- የመተንፈስ ችግር
- አዲስ የተከሰተ የጣዕም ወይም የማሽተት ስሜት ማጣት
- የጡንቻ ሕመም ወይም የሰውነት ሕመም
- የጉሮሮ ህመም
- ሳል (በሌላ የታወቀ ምክንያት የተነሳ ያልሆነ)
- ራስ ምታት እና ሌሎች ምልክቶች
- ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ ወይም ተቅማጥ (ማስመለስ፣ በጣም መታመም)
- ከባድ የድካም ስሜት እና ሌሎች ምልክቶች
- ከሌሎች ምልክቶች ጋር ተጨምሮ የአፍንጫ መታፈን ወይም የአፍንጫ ፍሳሽ (በሌሎች የታወቁ ምክንያቶች የተነሳ ያልሆነ)

### *በቅርቡ ጊዜ ክትባት ወስደዋል?*

ባለፉት 48 ሰዓታት ውስጥ ክትባት የወሰዱ ከሆነ፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ምልክቶች ሊታዩዎት ይችላሉ፡ ነገርግን አሁንም ወደ ትምህርት ቤት/ስራ መምጣት ይችላሉ።

- ትኩሳት፡ ከ100.0°F በታች
- ራስ ምታት
- ከባድ የድካም ስሜት
- ብርድ ብርድ ማለት
- የሰውነት ሕመም

ክትባት ከወሰዱ በኋላ እነዚህ ምልክቶች ለ 48 ሰዓታት ከቀጠሉ፡ እቤት ይቆዩ እንዲሁም በሐኪም ይመረመሩ።

# አዎንታዊ ውጤት ያላቸው ጉዳዮችን የሚገለሉበት የጊዜ ሰሌዳ

## ቀናት “1-5”

**ቀን "0" ምልክታዊ ምልክቶች የታዩበት ቀን ወይም የምርመራዎ አዎንታዊ ውጤት ያገኙበት ቀን ነው፡ ከሁለቱም የትኛውም ለመጀመርያ የተከሰተበት ቀን ነው።** ነርሷ ይህንን ውሳኔ ታደርጋለች።

ለተከታታይ 5 ቀናት ኳራንቲን ያድርጉ።

## “ቀን 6”፡- ወደ ስራ/ትምህርት ቤት ይመለሱ

**በ 6ኛው ቀን ወደ ትምህርት ቤት/ስራ መመለስ ይችላሉ :**
ቢያንስ ለ 24 ሰዓታት ያህል ከትኩሳት ነጻ ከሆኑ (ትኩሳትን የሚቀንሱ መድኃኒቶችን ሳይጠቀሙ) እንዲሁም የሕመም ምልክቶቹ በሙሉ ከሌሉ።

| አወንታዊ ውጤት ያገኙበት ቀን ወይም ምልክቶችን መታየት የጀመሩበት ቀን | ወደ ትምህርት ቤት ወይም ስራ የሚመለሱበት ቀን (የማግለል መጨረሻ) |
|---|---|
| ሰኞ | እሁድ* |
| ማክሰኞ | ሰኞ |
| እሮብ | ማክሰኞ |
| ሐሙስ | እሮብ |
| ዓርብ | ሐሙስ |
| ቅዳሜ | ዓርብ |
| እሁድ | ቅዳሜ* |

**6ኛው ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ፡ በሚቀጥለው ትምህርት ቤት ክፍት የሆነበት ቀን ይመለሱ።*

## ቀናት “6 - 10”

**ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሱ በኋላ በውስጥ እንዲሁም በውጭ ጭምብል ያድርጉ።**

**ለተወሰነ ጊዜ ከተገለሉ በኋላ የሚመለሱ ተማሪዎች አሉታዊ ምርመራ ውጤት ማሳየት አያስፈልጋቸውም፡** ነገር ግን የማያቋርጥ ምልክት ያለባቸው በነርሶቹ ውሳኔ እንደገና ይገመገማሉ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሄዱ ማድረግ ይቻላል።

ከተገለሉ በኋላ **በሚመለሱ ተማሪዎች ላይ CPS ፈጣን ምርመራዎች አያደርግም።**

# በየሳምንቱ የሚደረግ ምርመራ

ተማሪዎች እና ሰራተኞች ብየሳምንቱ የሚካሄድ ሁለት የኮቪድ ምርመራዎችን ማግኘት ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| ሰኞ | አንድ ጊዜ በትምህርት ቤት (ፑል) |
| ማክሰኞ | |
| እሮብ | |
| ሐሙስ | |
| ዓርብ | አንድ ጊዜ እቤት ውስጥ (ፈጣን የምርመራ) |

# አዎንታዊ የምርመራ ውጤቶት

የምርመራው አወንታዊ ውጤት ያገኙ፡ በ CPS የኮቪድ ፕሮቶኮሎች መሰረት ለ5 ተከታታይ ቀናት እቤት ውስጥ ይገለላሉ።

**አዎንታዊ የምርመራ ውጤት ለትምህርት ቤት ሪፖርት ማድረግ የትምህርት ቤቶቻችንን ደህንነት ለመጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው።**

- **ተማሪዎች፡-** መቅረትን ሪፖርት ለማድረግ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።
- **ሰራተኞች፡-** መቅረትን ሪፖርት ለማድረግ የበላይ አለቃዎን ያነጋግሩ።

# በቤት ውስጥ፡- ፈጣን የምርመራ

- ማንኛውም ተማሪ **የክትባት ሁኔታው ምንም ይሁን ምን** በአዲሱ የቤት ውስጥ ፈጣን የምርመራ ፕሮግራም መሳተፍ ይችላል።
- **የምርመራው ፕሮግራም በጎ ፈቃደኝነት የሚደረግ ነው።** በፍላጎት ለመሳተፍ እዚህ ላይ የመዘገቡ፡-CPS የቤተሰብ ፖርታል።
- የሚሳተፉ ተማሪዎች በየ 2 ሳምንቱ ኪት ይቀበላሉ፤ እያንዳንዱ ኪት የራስህን-ምርመራ ለማድረግ 2 መመርመርያዎች እና መመሪያዎችን ይይዛል።

# *ከትምህርት ቤት ውጭ አዎንታዊ የምርመራ ውጤት ያላቸው በተመለከተ፡ የቅርብ ተጠሪ አካል

የቅርብ ተጠሪ = በቀን ከ15 ደቂቃ በላይ ለኮቪድ ያለበት ግለሰብ መጋለጥ ከ3 ጫማ ባነሰ ርቀት ውስጥ

ወዲያውኑ ለርእሰ መምህሩን ያሳውቁ።

**የክትባት ሁኔታ፡-**

| | |
|---|---|
| ክትባት የወሰዱ እና የማበረታቻ ክትባት የወሰዱ<br><br>የተከተቡ እና የጨረሻው ክትባት መጠን ከመውሰድ ከ 5 ወር በፊት | • **በትምህርት ቤት ይቆዩ**<br>• በገለልተኛ ጊዜያቸው በበሽታው ከተለከፉ ሰዎች ጋር ሲገናኙ ጭምብል ያድርጉ።<br>• **የሚመከር፡-** በቤተሰብ ውስጥ አዎንታዊ የምርመራ ውጤት ከተገኘ ወይም ከቤተሰብ ውጭ ሆኖ በሕመሙ ከተለከፈ ሰው የተጋለጡ ከሆነ፡ የማግለል ጊዜው ካለቀ በኋላ **ከ 5-7 ቀናት** ያህል ይመረመሩ።<br>  ○ ከ 5-7 ኛው ቀን በትምህርት ቤት የመመርመር ፕሮግራም ጊዜ (ሰኞ/ማክሰኞ) ላይ ከሆነ፡ እንዲሁም የፈቃድ ቅጹ ከተጠናቀቀ በየሳምቱ በሚደረገው የፑል ምርመራ ላይ መሳተፍ ይችላሉ።<br>  ○ ከ 5-7 ኛው ቀን ከትምህርት ቤት የመመርመር ፕሮግራም ጊዜ ውጭ ከሆነ፡ በማህበረሰብ ውስጥ ወይም በቤት ውስጥ ፈጣን ምርመራ ያድርጉ።** CPS አሉታዊ የምርመራ ውጤት ማረጋገጫ አይፈለግም።<br>• **የበሽታ ምልክቶችን እንዳኖርዎት ይከታተሉ።** የሕመም ምልክቶች ከታዩ ወዲያውኑ ራስዎን ይገልሉ እና ይመርመሩ። |
| የተከተቡ እና የጨረሻው ክትባት መጠን ከወሰዱ ከ 5 ወር በኋላ<br><br>ያልተከተቡ ወይም እስካሁን ሙሉ በሙሉ ያልተከተቡ | • **ቀን 0-5** በመጋለጥ ቀጥሎ፡- **ኳራንቲን**<br>• **የሚመከር፡-** ለህመሙ ከተጋለጡ ከ 5 ቀናት በኋላ በማህበረሰብ ውስጥ ወይም በቤት ውስጥ ይመረመሩ (PCR ወይም ፈጣን ምርመራ)። CPS የአሉታዊ የምርመራ ውጤት ማረጋገጫ አይፈለግም፡ እንዲሁም ተማሪው ከተገለለበት ጊዜ ከተመለሰ በኋላ ፈጣን ምርመራ አያደርግም።<br>• **ቀን ከ 6 - 10፡-** ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጭምብሎች መልበስ አለበት።<br>• **የሚመለስበት ቀን፡-** ነርስ/የህዝብ ጤና ክፍል የጉዳዩ ዝርዝር ሁኔታ በመሰረት በማድረግ ይወሰናል።<br>• **የበሽታ ምልክቶችን እንዳኖርዎት ይከታተሉ።** የሕመም ምልክቶች ከታዩ ወዲያውኑ ራስዎን ይገልሉ እና ይመርመሩ። |

*CPS ወደ ከትምህርት ቤት ፈቃድ የተሰጣቸው ከትምህርት ጊዜ በኋላ አገልግሎቶች የሚሰጡ ተቋሞች የሚያጓጉዛቸው ተማሪዎች እንዲሁም በ CPS መገልገያዎች ውስጥ ከትምህርት ጊዜ በኋላ በሚቀርቡ ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ተማሪዎች እንደ "በትምህርት ቤት ውስጥ" የሚደረግ ግንኙነት ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ ገጽ ላይ ያሉት ፕሮቶኮሎች ለነዚያ ተማሪዎች አይመለከታቸውም።
**ለዚህ አላማ ቤተሰቦች በዓርብ ቀን ላይ በ CPS- የሚሰጠውን ፈጣን ምርመራ በቤት ውስጥ መደረግ ያለበት ሳምንታዊ ምርመራ ምትክ መጠቀም ይችላሉ።

# ጉዞ

| | ሙሉ በሙሉ ክትባት የወሰዱ ግለሰቦች | ክትባት ያልወሰዱ ግለሰቦች |
|---|---|---|
| **በአሜሪካ ውስጥ** | ከጉዞዎ በፊት እና ከተመለሱ ከ3-5 ቀናት በኋላ እንዲመረመሩ እንመክራለን።<br><br>የበሽታ ምልክቶችን እንዳኖርዎት ይከታተሉ። | |
| **በአለም አቀፍ** | አለም አቀፍ ጉዞ በተመለከተ የ CDC መመሪያዎችን ይከተሉ። ከጉዞዎ ወደ MA ከተመለሱ ከ3-5 ቀናት በኋላ እንዲመረመሩ እንመክራለን።<br><br>ለ 14 ቀናት የበሽታ ምልክቶችን እንዳኖርዎት ይከታተሉ። | ***ምርመራ አደርጋለሁ፦*** *ለተከታታይ 5 ቀናት ኳራንቲን ያድርጉ*<br>ከጉዞዎ ወደ MA ከተመለሱ በኋላ በ 6 ኛው ቀን፡ በማህበረሰብ ወይም በቤት ውስጥ። ቫይረሱ እንደሌልዎት ከተረጋገጠ በቀን 7 ላይ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይችላሉ። እባክዎን ቫይረሱ እንደሌልዎት የሚያሳይ ማስረጃ ለትምህርት ቤቱ ነርስ ያሳዩ።<br><br>የበሽታ ምልክቶችን እንዳኖርዎት ይከታተሉ።<br><br>***የኮቪድ ምርመራ አላደርግም፦*** *ለተከታታይ 10 ቀናት ኳራንቲን ያድርጉ*<br>በ 11 ኛው ቀን ወደ ትምህርት ቤት ይመለሱ።<br>የበሽታ ምልክቶችን እንዳኖርዎት ይከታተሉ። |